

# የሰብአዊ መብት ተፅዕኖ ትንታኔ

## ስለሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ረቂቅ ደንብ

**በኢፌዴሪ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ**
**የሕግና ፍትህ ጉዳዮች አማካሪ ጉባኤ**

**Legal and Justice Affairs Advisory Council**
**Federal Attorney General**

የበጎ አድራጎትና ማኅበራት የሕግ ማዕቀፍ የሥራ ቡድን

ግንቦት 26፣ 2012

# ማውጫ

**መግቢያ ....................................................................................................1**

**1. የሕግ ማሻሻያ ከተደረገ በኋላ የተመዘገቡ አዎንታዊ ለውጦች ....................................................1**

**2.የሰብአዊ መብት ተፅዕኖ ትንታኔን ለማከናወን አግባብነት ያላቸው ሕገ መንግስታዊና አለማቀፍ መስፈርቶች................................3**

**3. ረቂቅ ደንቡ ከሰብዓዊ መብት መለኪያዎች አንፃር.........................................................5**

3.1. የረቂቅ ደንቡ አዎንታዊ ጎኖችና የሚያስቀጥላቸው እምርታዎች.......................................... 5

3.2. በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ረቂቅ ደንብ ውስጥ ሊሻሻሉ የሚገባቸው ጉዳዮች....................................... 6

3.2.1. የፅሁፍ ድጋፍን በሚመለከት (አንቀፅ 3)............................................................... 6

3.2.2. በዝግ አካውንት ገንዘብ ስለማስቀመጥ (አንቀፅ 4(2))................................................. 7

3.2.3. ስለሙያ ማኅበራት (አንቀፅ 7(1)) ........................................................................ 7

3.2.4. ከመንግስት ጋር ተቀራርቦ ስለመስራት እና ድጋፍ (አንቀፅ 7(3)).......................................... 8

3.2.5. በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ሕጋዊ አስመስሎ ስለማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ ስለመርዳት (አንቀፅ 13) 9

3.2.6. ንብረት ሽያጭና ስጦታን በሚመለከት የተቀመጡ አዲስ ገደቦች እና አስተዳደራዊ ሸክሞች (አንቀፅ 14) ...... 10

ሀ. የሽያጭ ወይም የስጦታ ውልን ስለማሳወቅ (አንቀፅ 14(2)) ........................................... 10

ለ. የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ወይም ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን ተሽከርካሪዎች ስለመሸጥ (አንቀፅ 14(3))................ 11

ሐ. ንብረትን በስጦታ ስለማስተላለፍ (አንቀፅ 14(6))....................................................... 11

3.2.7. ለሶስተኛ ወገን ጥቅም በተቋቋሙ ድርጅቶች ላይ ስለሚደረግ ክትትል (አንቀፅ 15(6))........................... 12

3.2.8. ስለ ፕሮጀክት ስምምነት (አንቀፅ 21) ..................................................................... 12

3.2.9. ልዩ ድጋፍ የሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች (አንቀፅ 24) ...................................................... 12

3.2.10. ስለ ሲቪል ማኅበራት ፈንድ (አንቀፅ 25) ................................................................ 13

## መግቢያ

የሕግና ፍትህ ጉዳዮች አማካሪ ጉባኤመንግስት በሲቪል ማኅበረሰብድርጅቶች ዙሪያ ማድረግ ያለበትን ለውጥ በሚመለከት ቴክኒካዊ ምክረ-ሀሳብ ለማቅረብ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ሕግ ማሻሻያ የሥራ ቡድን ማቋቋሙ ይታወሳል። የስራ ቡድኑ አባላት ባብዛኛው ከሲቪል ማኅበረሰብ ዘርፍ የተውጣጡ ሲሆን የሕግ ባለሙያዎች፣ ምሁራን፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች መሪዎች እንዲሁም ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት አማካሪዎች የተካተቱበት መሆኑ ከሥራ ቡድኑ ጥንካሬዎች መሃል በዋናነት የሚጠቀስ ነው።

የሥራ ቡድኑ ከተቋቋመ በኋላ በሥራላይየነበረውን "የበጎ አድራጐቶችና የማኅበራት አዋጅ ቁጥር 621/2001" አተገባበርና ተያያዥ ጉዳዮችን የሚዳስስ ጥናት አካሂዶ በጥናቱ ግኝት መሠረት ባቀረበው ምክረ ሃሳብ አዲስ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ሕግ ረቂቅ ተዘጋጅቶ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ አዋጅ ቁጥር 1113/2011 ሆኖ መጽደቁ ይታወሳል። በዚህ ሂደት የጥናት ቡድኑ በመላው ሃገሪቱ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ያወያየ ሲሆን ሕጉ የመደራጀት መብትን የተመለከቱ ዓለም ዓቀፍና አህጉራዊ፣እንዲሁም ሕገ-መንግስታዊ መርሆዎችን ባገናዘበ መልኩ ተዘጋጅቷል።

የሕግና ፍትህ ጉዳዮች አማካሪ ጉባኤ የመጀመሪያው ዓመት የስራ ዘመን ከተጠናቀቀ በኋላ አማካሪ ጉባዔው ትኩረቱን ለሰብዓዊ መብት፣ ዴሞክራሲ እና የሕግ የበላይነት መረጋገጥ አይነተኛ ሚና የሚያበረክቱ የማሻሻያ ፓኬጆችን አፈፃፀም መደገፍና መመዘን ላይ ትኩረቱን አድርጓል። ይህ ስራ አማካሪ ጉባዔዉ ባቀረባቸው የመፍትሔ ሀሳቦች መሰረት የተደረጉ ማሻሻያዎች ምን ያህል ተቀባይነት እንዳገኙ እና በስራ ላይ ሲውሉም ያስከተሉትን ተፅዕኖ በመከታተልና በመገምገም ባጠቃላይ አፈፃፀማቸውን መመዘንን እንዲሁም የማሻሻያ ሂደቱ ግቡን ይመታ ዘንድ ለአስፈፃሚ አካላት ክትትል እና ተቋማዊ ድጋፍ የማድረግ ስራዎችን ያካትታል። የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን ረቂቅደንብ በሚመለከት የሥራቡድኑ ያዘጋጀው የሰብአዊ መብት ተፅዕኖ ትንታኔ አማካሪጉባዔው የአፈፃፀም ድጋፍና ምዘና አካል ሲሆን ይህ ትንታኔ የተጠናቀረው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1113/2011ን ተፈፃሚነት እንደሚደግፍ በማሰብ ነው።

## 1. የሕግ ማሻሻያ ከተደረገ በኋላ የተመዘገቡ አዎንታዊ ለውጦች

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1113/2011 መፅደቁን ተከትሎ በቀድሞው የበጐ አድራጐቶችና የሲቪል ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 621/2001 ተካተው የነበሩ የማያሰሩ ድንጋጌዎች የመደራጀት መብትን የተሻለ ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችሉና ለሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እንቅስቃሴ ምቹ ሁኔታን በፈጠሩ ድንጋጌዎች እና አሰራሮች ተተክተዋል። አዋጁ ከፀደቀ ገና አንድ አመት አካባቢ ብቻ ቢሆንም በዘርፉ ከፍተኛ የሆነ መነቃቃት እና አዎንታዊ ለውውጦች እንዲመዘገቡ አስችሏል። አዋጁ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች፣ ለጋሾች (donors)፣ መንግስት እና ሰፊው ማኅበረሰብ ዘርፉ ዴሞክራሲያዊት እና የሕግ የበላይነት የሰፈነባት ኢትዮጵያን ለመገንባት ሊጫወት የሚገባውን ሚና በመገንዘብ የተሻለ ተነሳሽነት እንዲያድርባቸው እና ተግባራዊ እንቅስቃሴም እንዲያደርጉ ያስቻለ ነው።

አዋጅ ቁጥር 1113/2011 በመጀመሪያ ደረጃ ያስመዘገበው አዎንታዊ ለዉጥ ከዚህ በፊት በከፍተኛ ሁኔታ ተሸርሽሮ በነበረው የመደራጀት መብት ላይ የተጣሉ ዘርፈ ብዙ ገደቦችን ማስቀረቱ ነው። የነዚህ ገደቦች መነሳት በሀገሪቱ የመብቶችና የዲሞክራሲ እድገት ላይ የሚኖረው አዎንታዊ ተፅዕኖ በቀጣይ አመታትና አስርተ አመታት የሚታይ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የለውጡ የአጭር ጊዜ ውጤት እንደ አዲስ ዘርፉን የሚቀላቀሉ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ቁጥር እንዲጨምር ማስቻሉ ነው። ይኸውም አዋጁ ከፀደቀበት መጋቢት 2011 ዓ/ም ጀምሮ እስከ የካቲት 2012 ዓ/ም ድረስ ባለው አንድ አመት ውስጥ 600 አዲስ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ተመዝግበዋል። ይህ አሀዝ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በአመት ውስጥ ይመዘገቡ ከነበሩ ድርጅቶች አንፃር ከፍተኛ ከመሆኑም ባሻገር አዲስ የተመዘገቡት ድርጅቶች ባብዛኛው ሰብዓዊ መብት ላይ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ መሆናቸው ለዉጡን ልዩ ያደርገዋል።

በተጨማሪም 1,800 የሚደርሱ ነባር የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በአብዛኛው አላማቸውን መብት ላይ ትኩረት በማድረግ እንደገና ተመዝግበዋል። አዋጁ መውጣቱን ተከትሎ በቀድሞው ሕግ እና አሳሪ አሰራሮች ምክንያት ሰብአዊ መብቶች፣ እና ዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ላይ እንዳይሰሩ ተገድበው የነበሩ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የአላማ ለውጥ በማድረግ በሰብዓዊ መብቶች ላይ በመስራት ላይ ይገኛሉ። ማሻሻያውን ተከትሎ አንዳንድ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ከእርዳታ ሰጭነት በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ እና የሕግ የበላይነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የፖሊሲ ሃሳቦችን ወደ ማመንጨት በመሸጋገር ላይ ይገኛሉ። ለአብነት ያክል በአማራ ብሄራዊ ክልል ደሴ ማረሚያ ቤት ስር የሚገኙ ሴት ታራሚዎችን እና ልጆቻቸውን አያያዝ በሚመለከት የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ያቀረቡት ሀሳብ እና ስትራቴጅ ከደሴ ማረሚያ ቤት ባሻገር በክልሉ ምክር ቤት ተቀባይነት በማግኘቱ ሕግ ሆኖ ሊወጣ ተቃርቧል። በተመሳሳይ ሁኔታ በድሬዳዋ አስተዳደር በአስተዳደሩ ስር የሚገኙ ሆስፒታሎች እና ጤና ጣቢያዎች የሱስ ተጠቂዎችን የሚከታተል ምንም አይነት የሰው ሀይል አደረጃጀትም ይሁን የገንዘብ አቅርቦት ያልነበራቸው ሲሆን በአካባቢው የሚሰሩ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባቀረቡት ሀሳብ እና ባደረጉት ግፊት ምክንያት አስተዳደሩ የ 3 ሚሊዮን ብር በጀት መድቦ በዘላቂነት ስራ መስራት ጀምሯል።

አዋጁ አዎንታዊ ተፅእኖ የፈጠረው በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ላይ ብቻ ሳይሆን በለጋሾች ላይም ከፍተኛ መነሳሳትን ፈጥሯል። በቀድሞው ሕግ ምክንያት ዘላቂ ለውጥ የማያመጡ የበጎ አድራጎት ስራዎችን ይደግፉ የነበሩ እንደ ዩኤስኤድ፣ የአውሮፓ የሲቪል ማኅበራት ፈንድ፣ እና የኢትዮጵያ ማኅበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራም ያሉ ለጋሾች ማሻሻያውን ተከትሎ መብት ላይ የሚሰሩ ድርጅቶችን መደገፍ ላይ ትኩረታቸውን አድርገዋል። ይህ ደግሞ ጠንካራ እና በዘላቂነት ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ላይ የሚሰሩ ድርጅቶች እንዲፈጠሩ የሚያስችል ነው።

አዋጁ ከወጣ በኋላ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲን ጨምሮ የተለያዩ የመንግስት አካላት ለዘርፉ ያላቸው አተያይ የተሻሻለ ሲሆን አዋጁን ለማስፈፀም ከፍተኛ ተነሳሽነት እንዳላቸው በተደረጉት ውይይቶች እና በተግባር በሚያደርጉት እንቅስቃሴ አረጋግጠዋል። በክልሎች ደረጃም ኦሮሚያን እና ደቡብን የመሳሰሉ አንዳንድ ክልሎች ማሻሻያውን በተሻለ ሁኔታ ለመተግበር እንቅስቃሴ ጀምረዋል።

ስለሆነም በዚህ ደረጃ በዘርፉ ላይ ከፍተኛ አዎንታዊ ለውጦችን የፈጠረውን አዋጅ ለማስፈፀም የሚወጣው ደንብ በአዋጁ የተፈጠሩትን አዎንታዊ ለዉጦች ወደ ላቀ ደረጃ የሚያደርስ ሊሆን እንደሚገባ ታሳቢ ማድረጉ አግባብ ነው። ይህ የሰብዓዊ መብት ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 1113/2011ን ለማስፈፀም የተዘጋጀውን ረቂቅ ደንብ ከላይ የተመዘገቡ ለዉጦችን ከማስቀጠል እና ከአለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት መስፈርቶች አንፃር የሚመረምር ይሆናል።

## 2.የሰብአዊ መብት ተፅዕኖ ትንታኔን ለማከናወን አግባብነት ያላቸው ሕገ መንግስታዊና አለማቀፍ መስፈርቶች

አለም አቀፍ የሰብዐዊ መብት መስፈርቶች እና አሰራሮች በዚህ ደንብ የተቀመጡ ገደቦችን ተገቢነት ለመመዘን ባለ ብዙ ደረጃ ሰፊ የመመዘኛ ዘዴዎች ስራ ላይ መዋል እንዳለባቸው ያስቀምጣሉ። ይህ የመመዘኛ ዘዴ በአለም አቀፉ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀፅ 22 ስር በግልፅ ተቀምጦ ይገኛል። የአፍሪካ የሰዎች እና የህዝቦች መብት ኮሚሽን የገደቦችን ተገቢነት ለመመዘን ገደቡ “በሕግ የተደነገገ” ስለመሆኑ፣ ገደቡ “ቅቡልነት ያለው የህዝብ ጥቅምን” ለማስከበር የተደረገ ስለመሆኑ፣ ገደቡ “ለዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ” “ፍፁም አስፈላጊ” ስለመሆኑ እንዲሁም ለማሳካት ከታሰበው የህዝብ ጥቅም አንፃር የሚደረገው ገደብ “ተመጣጣኝ” ስለመሆኑ ጥልቅ ትንተና ማድረግ እንደሚያስፈልግ ያብራራል[1]። ከነዚህ የመመዘኛ መስፈርቶች መካከል የተወሰኑት በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት በግልፅ ዕውቅና የተሰጣቸው ሲሆን በተዘዋዋሪ ደግሞ በአንቀፅ 9(4) እና አንቀፅ 13 (2) መሰረት ዕውቅና ተሰጧቸዋል[2]። በተጨማሪም የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት የዴሞክራሲ፣ የሕገ-መንግስታዊነት እንዲሁም የሕግ የበላይነት መርሆዎችን የተቀበለ በመሆኑ ምክንያት የሰብአዊ መብቶች አተረጓጎም አካል የሆኑ[3] “አለም አቀፍ ሕገ መንግስታዊ መስፈርቶች” ወይም “የተለመዱ የአለም አቀፍ ሕገ መንግስታዊ ቋንቋዎች[4]” ረቂቅ ደንቡን በመመዘን ሂደት ተፈፃሚ እንዲሆኑ ያስገድዳል።

ባጠቃላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የምዘና ስርአት ባለ ሦስት ደረጃ የትንተና ሂደትን የሚያካትት ሲሆን የአንደኛው አለመሟላት የመብት ጥሰት ወይም ገደብ ስለመኖሩ ማረጋገጫ ነው። **<u>የመጀመሪያው የትንተና ደረጃ</u>** በመብቱ ላይ የሚደረገው ጥሰት ወይም ገደብ በሕግ በግልፅ የተቀመጠ መሆኑን ወይም አለመሆኑን የሚመለከት ነው። በተጨማሪም በመብቱ ላይ ሊደረጉ ስለሚችሉ ጥሰቶች ወይም ገደቦች የሚወጣው ሕግ ሊደረጉ የታሰቡ ጥሰቶች ወይም ገደቦች የሕግ ጥሰት ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለውን ለመመዘን በሚያስችል ደረጃ ለህዝብ ግልፅ ስለመሆናቸው ይተነተናል።[5] **<u>ሁለተኛው የትንተና ደረጃ</u>** ሕጉ ገደቦችን ያደረገው በሕገ መንግስቱ ወይም አለም አቀፍ ስምምነቶች በተቀመጡ ልዩ ሁኔታዎች መሰረት ቅቡልነት ያለውን ጥቅም ለማስከበር መሆን ወይም አለመሆኑን መመርመር ነው። **<u>ሦስተኛው የትንተና ደረጃ</u>** ደግሞ “የተመጣጣኝነት ትንተና” ሲሆን በስሩ የተለያዩ መለኪያዎችን ያቀፈ ነው። የመጀመሪያው የሚደረገው ገደብ ተስማሚነት ወይም ውጤታማነት መለኪያ ሲሆን

---

[1] *እነዚህን መርሆዎች በሚመለከት ጠቅለል ያለ ሀተታ ለማግኘት ሞሚን ኢጋክ* (*Monim Elgak*)*፣ ኦስማን ሁሜዳ* (*Osman Hummeida*) *እና ኦሚር ሱሊማን* (*Amir Suliman*) (*በኤፍዲኤች* (*FIDH*) *እና በኦኤምሲቲ* (*OMCT*) *ከ ሱዳን ጋር ያደረጉት ክርክር፣ ኮም ቁጥር* (Comm. No).379/09 Afr. Comm’n (2014) *አናቅጽ*. 114, 118; *Interights, በአፍሪካ የሰባዊ መብት እና ልማት ኢንስቲትዩት* (*Institute for Human Rights and Development in Africa*) *እና Association Mauritanienne des Droits de l’Homme v. Mauritania*, Comm. No. 242/01 Afr. Comm’n (2010), *አንቀፅ*-78.

[2] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግስት፣ አዋጅ ቁጥር 1/1995 ፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ፣ አንቀፅ 15, 17, 18 (4), 19 (6), 20 (3), 22, 23, 26 (3), 27 (5), 29 (6) እና (7), 30, 31, እና 40.

[3] Aharon Barak, <u>PROPORTIONALITY: CONSTITUTIONAL RIGHTS AND THEIR LIMITATIONS</u>), *ገፅ*- 213-241 (Cambridge Univ. Press, 2012) እና ሮበርት አሌክሲ (Robert Alexy)፣*Constitutional Rights Balancing and Rationality*, 16 Ratio Juris 131, passim (2003).

[4] በተከታታይ፣ Alec Stone Sweet እና Jud Mathews, *Proportionality Balancing እና Global Constitutionalism*, 7 Columbia J. of Transnat. L. 73, 80 እና*passim* (2008); እናMoshe Cohen-Eliya እና Iddo Porat, *Proportionality and the Culture of Justification*, 59 Am. J. Comp. L. 463, 466 (2011); Barak, *supra* note **Error! Bookmark not defined.**,ገፅ 175-206 *ተመልከት*.

[5] አለም አቀፉ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት፣ (1966) ፣ አንቀፅ- 12፣ 17፣ 18፣ 19 ፣ እና 22

ይህ መለኪያ በሚደረገው ገደብ እና በገደቡ እንዲሳካ በሚፈለገው ግብ መካከል ምክንያታዊ የሆነ ግንኙነት እንዲኖር ያስገድዳል። በዚህ የትንተና ደረጃ ውስጥ ሁለተኛው መለኪያ የአስገዳጅ ሁኔታ መኖር ሲሆን ይህ መለኪያ ስለ ገደቦች የሚወጣ ሕግ ቅቡልነት ያለውን አላማ ለማሳካት ከሚያስፈልገው በላይ ክልከላዎች ማድረግ እንደሌለበት ያስቀምጣል። ሦሥተኛው መለኪያ “የተመጣጣኝነት ምዘና” ሲሆን ይህ መለኪያ ሕጉ አስፈላጊ እና ተመጣጣኝ ከሆነው በላይ መብቶችን መገደብ እንደሌለበት ያስቀምጣል።




ከላይ የተቀመጡትና በዚህ የሰብአዊ መብት ተጽዕኖ ትንታኔ ጥቅም ላይ የዋሉት አጠቃላይ የምዘና መርሆች በዚህ ምስል በተቀመጠው መሰረት ሊጠቃለሉ የሚችል ሲሆን የአፍሪካ ኮሚሽን እንደ ኢትዮጵያ ያሉ የሲቪል ማህበረሰብ ሕጎችን ለሚያወጡ እና የሚያሻሽሉ ሀገራትን ለመደገፍ በማሰብ በአፍሪካ የመደራጀት እና የመሰብሰብ ነፃነትን በሚመለከት ያዘጋጀው መመሪያም[6] ይህን ረቂቅ አዋጅ ለመተንተን ጥቅም ላይ ውሏል። የስራ ቡድኑ ይህ ሪፖርት ደንቡን እያረቀቀ ላለው ለሲቪል ማኅበራት ኤጀንሲ ብቻ ሳይሆን አስፈፃሚ ተቋማት ደንቦችን ከአዋጆች፣ ከሕገ መንግስቱ እንዲሁም አለም አቀፍ ስምምነቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ ለማዘጋጀት ከፍተኛ ጥቅም እንደሚኖረው ተስፋ ያደርጋል።

---

[6] African Commission on Human and Peoples’ Rights, Guidelines on Freedom of Association and Assembly in Africa (21 Sept. 2017)የአፍሪካሰብዓዊእናየህዝቦችመብትኮሚሽን፣በአፍሪካየመደራጀትእናየመሰብሰብነፃነትመመሪያ [ከዚህ ብኋላ “በአፍሪካየመደራጀትእናየመሰብሰብነፃነትመመሪያ”]።

## 3. ረቂቅ ደንቡ ከሰብዓዊ መብት መለኪያዎች አንፃር

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1113/20011 እና ረቂቅ ደንቡ በቀድሞው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 621/2001 ስር የነበሩ የማያሰሩ ድንጋጌዎችን በማስቀረት ከፍተኛ ማሻሻያ አድርጓል። በዚህ ክፍል ውስጥ የሕግ ማሻሻያው ያደረጋቸው መልካም የሚባሉ ዋና ዋና ማሻሻያዎች በዚህ የሰብአዊ መብቶች ተፅዕኖ ግምገማ ትንታኔ ለመዳሰስ ተሞክሯል። በሌላ በኩል ረቂቅ ደንቡ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1113/2011 ለማስፈፀም የተዘጋጀ እንደመሆኑ መጠን ረቂቅ ደንቡ ከአዋጁ እንዲሁም ከሰብዓዊ መብቶች እና ሕገ መንግስት መርሆዎች ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ሊሰሩ የሚገቡ ስራዎች በዝርዝር ተተንትነዋል።

### 3.1. የረቂቅ ደንቡ አዎንታዊ ጎኖችና የሚያስቀጥላቸው እምርታዎች

የቀድሞው የሲቪል ማኅበራት እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 621/2001 ዋና አላማ የማሕበረሰቡን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ በተለይ ደግሞ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎቹን መቆጣጠር ላይ ያጠነጠነ ነበር። በአንፃሩ ደግሞ ሕገ-መንግስታዊ የሆነውን የመደራጀት ነፃነት በስልጣን ላይ ለነበረው ስርዓትቀጣይነትና ምቾት ብሎ መስዕዋት ያደረገ ነበር። አዋጅ ቁጥር 1113/2011 እና ረቂቅ ደንቡ በቀድሞው ሕግ የነበሩ የማያሰሩ ድንጋጌዎችን ያስቀረ እና ባጠቃላይ የነበረውን ሁናቴ የቀየረ ሲሆን ይህ ደንብ አዋጁ ያመጣቸውን ዋና ዋና በጎ የሕግ ለውጦች ማስቀጠሉ ዋነኛው ጥንካሬው ነው።ከሕገ መንግስታዊና አለማቀፍ መስፈርቶች አንጻር በአዋጅ ቁጥር 621/2001አዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሃል ያለው ልዩነት እጅግ በርካታ ከመሆኑ አንፃር የተወሰኑ ማሳያዎችን ማንሳት በቂ ነው።

አዋጅ ቁጥር 621/2001 በአንቀፅ 64 (2) እና 65 (4) ማንኛውም የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት በሦሥት ወራት ውሥጥ መመዝገብ ዕንዳለበት የሚያስገድድ ሲሆን በዚህ ጊዜ ውሥጥ ካልተመዘገበ ግን እንደሚፈርስ ይደነግጋል። ይህ ድንጋጌ መደበኛ ያልሆኑ እና ብዛት ያላቸው የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች በመንግስት ካልተመዘገቡ በስተቀር ሕገ ወጥ ድርጅቶች እንዲሆኑ ያደረገ ነው። ይህ ደግሞ መንግስት በተግባር ሁሉንም አደረጃጀቶች መመዝገብ ስለማይችል ማን የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት አባል መሆን እንዳላበት እና እንደሌለበት የመከልከል ስልጣን ሰጥቶት ቆይቷል። የቀድሞው አዋጅ አስፈፃሚው አካል ምዝገባ በማድረግ፣ ገቢ በማሰባሰብ፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን የውስጥ ጉዳዮች በመበርበር እንዲሁም ድርጅቶቹን በመዝጋት ጉዳዮች ላይ ያልተገደበ እና ፍፁማዊ ፈቃደ-ስልጣን እንዲኖረው የሚያደርግ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ አዋጅ ቁጥር 621/2001 በአንቀፅ 68 ስር ለምዝገባ የሚቀርብ ማመልከቻ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ ከሚጠይቃቸው ማናቸውም ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ እንዳለበት በመደንገግ ለመንግስት በሕግ ያልተገደበ ስልጣን ሰጥቶታል። ደንብ ቁጥር 168/2009(አንቀጽ 3 (1)) የመንግስትን ስልጣን ካለመገደቡም ባሻገር ተጨማሪ ግልጽ ያልሆኑና ምዝገባን የሚያከብዱ ቅድመ-ሁኔታዎች በመጨመር ችግሩን እንዳባባሰው ማስተዋል ይቻላል።

የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1113/2011 በአንፃሩ በአንቀፅ 6 ስር በቀድሞው አዋጅ የነበረውን የመንግስት ያልተገደበ ስልጣን በማስቀረት የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ ሚና ድርጅቶችን መደገፍ፣ ሥራቸውን ማሳለጥና ማስተባበር እንዲሆን አድረጓል። ይህም በቀድሞው ሕግ መንግስት ስለ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የነበረውን አመለካከት እና ሚና የቀየረ ነው። አዲሱ ደንብ አዲሱን የሕግ አቅጣጫ ከማስቀመጡ በተጨማሪ ግልጽ በሆነ ቋንቋ “የበጎ አድራጎት

ድርጅቶችን ለመመዝገብና ለማስተዳደር የወጣው ደንብ ቁጥር 168/2009 በዚህ ደንብ ተሽሯል” ብሎ መደንገጉ በተግባር ላይ የሚታዩ ግልጽ ያለመሆን ሁኔታና ችግር ያለባቸውን ከድሮው ሕግ የሚመነጩ አሰራሮችን ከማስወገድ አንፃር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።ሌላው እና ዋነኛው አዋጅ ቁጥር 621/2001 የኅብረተሰቡን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ለመቆጣጠር የተጠቀመው ዘዴ ገቢያቸውን ከኢትዮጵያ ውጭ የሚያገኙ ድርጅቶች በሰብዓዊ መብቶች፣ በግጭት አፈታት እንዲሁም በምርጫ ትምህርት እና ታዛቢነት ዙሪያ እንዳይሰሩ መከልከሉ ነው።

በአንፃሩ የአዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀፅ 57(7) ከገኙው ፓርቲ ጋር ግንኙነት ያላቸው“ኢትዮጵያውያንየብዙሀን ማኅበራት” በማንኛውም ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ እንዲሳተፉ በመፍቀድ አድሎአዊ አሰራሮችን ፈጥሮ ቆይቷል። አዋጅ ቁጥር 1113/20011 በቀድሞው ሕግ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በሰብዓዊ መብቶች እና መልካም አስተዳደር ላይ እንዳይሰሩ ገድቦ የቆዩትን ድንጋጌዎች በመሻር ይልቁንም የሚያሰሩ ድንጋጌዎችን አካትቷል። ረቂቅ ደንቡ ይህንና ሌሎች ከሕገ መንግስቱ ጋር የሚጣጣሙና በአዋጅ ቁጥር 1113/20011 የተደነገጉትን የህግ መርሆችንና አሰራሮች ከማስቀጠልም አልፎ ማጠናከሩ እንደሚበረታታ መጠቆሙ ተገቢ ነው።

## 3.2. በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ረቂቅ ደንብ ውስጥ ሊሻሻሉ የሚገባቸው ጉዳዮች

### 3.2.1. የፅሁፍ ድጋፍን በሚመለከት (አንቀፅ 3)

የረቂቅ ደንቡ አንቀፅ 3(1) “ከኤጀንሲው ድጋፍ የሚፈልግ ማንኛውም በመመዝብ ሂደት ላይ ያለ ድርጅት መስራች ከምዝገባው ጋር የተያያዙ አስፈላጊ ተግባራትን ለማከናወን ከኤጀንሲው የፅሁፍ ድጋፍ እንዲሰጠው መጠየቅ” እንደሚችል ይገልፃል። ይህ አይነቱ የድጋፍ ደብዳቤ በሲቪል ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 1113/2011 ያልተካተተ አዲስ ድንጋጌ ሲሆን የድጋፍ ደብዳቤው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በምዝገባ ሂደት ውስጥ ስራቸውን ለማከናወን እንደ ቅድመ ሁኔታ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ አለባቸው ወይ የሚለው ግልፅ አይደለም። ይህ ድንጋጌ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ለምዝገባ ማሟላት ያለባቸው ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታ ተደርጎ ሊተረጎም ስለሚችል በድርጅቶች ላይ አላስፈላጊ ተፅዕኖ ሊፈጥር የሚችል ነው።

ይህ ድንጋጌ እንደ ቅድመ ሁኔታ አይተረጎምም ተብሎ ቢታሰብ እንኳን ድንጋጌው አላስፈላጊ (superfluous) ከመሆኑ አንጻር የአንቀጹ አስፈላጊነት አጠያያቂ ነው። በሌላ አነጋገር የአንቀጹ እንደ ፈቃጅ ድንጋጌ ታይቶ ተጨማሪ ቅድመሁኔታአይጭንም ቢባል ኤጀንሲው ለማናቸውም በየትኛውም ሂደትላይላለ ድርጅት የፅሁፍ ድጋፍ መስጠትን የሚከለክል ህግ ካለመኖሩ አንጻር አላስፈላጊ (superfluous) ድንጋጌ ስለሚሆን በረቂቁ ውስጥ መካተቱ አስፈላጊ አይሆንም። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን ረቂቅ ደንቡ ይህን አንቀጽ ይዞ ቢታተም ድንጋጌው በህግ አተረጓጎም ደንብ እንደቅድመሁኔታአይተረጎምም ተብሎ ቢታሰብ እንኳን በአተረጓጎሙ ሂደት አስፈጻሚ አካላት ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታ እንደሚጭን አድርገው ቢወስዱት/ቢተረጉሙት በድርጅቶች ላይ አላስፈላጊ ተፅዕኖ መፍጠሩ ወይም ተፅዕኖ የሚፈጠርበት እድል መከፈቱ አይቀሬ ነው። ከዚህ አንጻር አንቀጹ ቢያንስ አላስፈላጊ (superfluous)፣ ልቅና ለትርጉም ተጋላጭ ሲሆን ቢበዛ ደግሞ የድጋፍ ደብዳቤ የማቅረብ ቅድመ ሁኔታን የሚጭን ተደርጎ ሊወሰድ የመቻል እድል አለው። ከሁለቱም አተረጓጎሞች አንጻር ሲታይ ድንጋጌው የመደራጀት መብት ላይ አግባብነት የሌለው ጫና ሊፈጥር የሚችል ስለሆነ ቀሪ ሊደረግ ይገባል።

በተጨማሪም፣ አንቀፁ ግልፅነት ስለሚጎድለው በአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት መስፈርቶች በመደራጀት ነፃነት ላይ የሚደረግ ገደብ “ግልፅ በሆነ ሕግ መደንገግ” አለበት የሚለውን መስፈርት አያሟላም። በረቂቅ ደንቡ አንቀፅ 3 (1) የሚታየው የግልፅነት

ችግር የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምን መስራት እንዳለባቸው ብዥታን በሚፈጥር ደረጃ መሆኑ ደግሞ ድንጋጌው ከአለም አቀፍ መስፈርቶች አንፃር ሲታይ ከፍተኛ ክፍተት ያለበት መሆኑን የሚያሳይ ነው። ስለሆነም አንቀፅ 3 ከረቂቅ ደንቡ ቢወጣ የተሻለ ነው።

### 3.2.2. በዝግ አካውንት ገንዘብ ስለማስቀመጥ (አንቀፅ 4(2))

ረቂቅ ደንቡ በአንቀፅ 4(2) የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት ለመመስረት ያሰበ ሰው ወይም ሕጋዊ ወኪሉ ለበጎ አድራጎት አላማ ሊያውል የፈለገውን የገንዘብ መጠን ገንዘቡን ሊያቋቁም በታሰበው ድርጅት ስም ወይም በኤጀንሲው ዝግ አካውንት ማስገባት ይኖርበታል የሚል ቅድመ ሁኔታ ያስቀምጣል። ይሁን እንጅ ይህ አስገዳጅ ቅድመ ሁኔታ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት ለማቋቋም በሚያስቡ ሰዋች ላይ አላስፈላጊ ጫና በማድረግ ብዛት ያላቸው የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቶች እንዳይኖሩ የሚያደርግ ሲሆን በኤጀንሲው ላይም ተጨማሪ ጫና የሚፈጥር ነው። ረቂቅ ደንቡ በጥቅሉ አመልካቾች አካውንት እንዲከፈትላቸው በጠየቁ ጊዜ ኤጀንሲው ለባንክ ደብዳቤ ይፅፋል ከማለት በዘለለ ደብዳቤ ለማግኘት ስለሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች እና የጊዜ ገደቦች ዝርዝር ቅድመ ሁኔታዎችን ባለማስቀመጡ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት የሚቋቋሙ ሰዎች ሕጉን ማሟላታቸውን ወይም አለማሟላታቸውን ለማወቅ ይቸገራሉ። በተጨማሪም ረቂቅ ደንቡ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት በጥሬ ገንዘብ ብቻ ሳይሆን ንብረት በመስጠትም የሚመሰረት መሆኑን የዘነጋ ስለሆነ፣ንብረታቸውን በመሰጠት የዘለቄታ በጎአድራጎት ድርጅት ለመመስረት የሚፈልጉ ሰዎችን መብት የሚገድብ ነው።

ረቂቅ ደንቡ በአዋጁ ያልተካተቱ በተለይምአዲስ ግዴታን የሚጭን ድንጋጌ ማካተቱ በራሱ የህጋዊነትና ሕገ መንግስታዊነት ጥያቄዎችን ከማስነሳቱ በተጨማሪ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት የሚያቋቋሙ አካላት በዝግ አካውንት ገንዘብ እንዲያስቀምጡ እና አካውንት ለመክፈት ከኤጀንሲው ፈቃድ እንዲጠይቁ ማስገደድ በአለም አቀፍ ስምምነቶች መብቶች ሊገደቡ ከሚችሉበት አራቱ የመንግስት ጥቅሞች ማለትም ብሔራዊ ደህንነትን፣ የህዝብን ደህንነት፣ የህዝብን ሞራልና ጤና ወይም የሌሎችን መብት ከመጠበቅ አኳያ አንዱንም የሚያሟላ አይደለም። አለም አቀፉ የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ስምምነት እንዲሁም የአፍሪካ የሰዎች እና የህዝቦች ቻርተር በመደራጀት ነፃነት ላይ የሚደረግ ማንኛውም ገደብ "በአንድ ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ውስጥ ከላይ የተገለፁትን አራቱ የመንግስት ጥቅሞች ለማሳካት አስፈላጊ" መሆን እንዳለበት ያስቀምጣሉ። ስለሆነም ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ከመገንባት አንፃር ይህ የደንቡ አንቀፅ ቢወጣ የተሻለ ነው።

### 3.2.3. ስለሙያ ማኅበራት (አንቀፅ 7(1))

ረቂቅ ደንቡ በአንቀፅ 7 ስር "ሙያ" ማለት ከአንድ በመንግስት እውቅና ካገኘ የትምህርት ተቋም በአንድ ሙያ ዙሪያ ስላለ እውቀት፤ ልምድ ወይም ክህሎት የሚሰጥ የትምህርት ማስረጃ ወይም ሌላ ሙያን ማረጋገጥ በሚችል የመንግስት አካል ወይም ስልጣን ባለው አካል የተረጋገጠ ሙያ ማለት ነው በሚል ይገልፀዋል። ይሁን እንጅ ይህ ትርጉም በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ለሙያ ማኅበራት ከተሰጠው ትርጉም በላይ ገዳቢ ከመሆኑም ባሻገር በመደራጀት ነፃነት ላይ አላስፈላጊ ተፅእኖ የሚያሳድር ነው።

ማንኛውም ሰው የሙያ ማኅበር አባል ለመሆን ከታወቀ ተቋም፣ ከመንግስት ወይም ከሌላ የታወቀ አካል የትምህርት ማስረጃ እንዲያቀርብ የሚገደድበት ቅድመ ሁኔታ በአዋጁ ያልተቀመጠ ተጨማሪ ጫና ከማምጣት በዘለለ ምንም አይነት ቅቡልነት ያለው አላማን አያሳካም። ይህ ቅድመ ሁኔታ "በአንድ ዴሞክራሲያዊ ማኅበረሰብ" ውስጥ አስፈላጊ ገደብ ካለመሆኑም በላይ

አራቱ የመንግስት አላማዎች ማለትም ብሔራዊ ደህንነትን፣ የህዝብን ደህንነት፣ የህዝብን ሞራልና ጤና ወይም የሌሎችን መብት ከመጠበቅ አኳያ አንዱንም የሚያሟላ አይደለም። አለም አቀፉ የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ስምምነት እንዲሁም የአፍሪካ የሰዎች እና የህዝቦች ቻርተር በመደራጀት ነፃነት ላይ የሚደረግ ማንኛውም ገደብ በአንድ ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ውስጥ አራቱን የተፈቀዱ የመንግስት ጥቅሞች ለማስከበር መሆን እንዳለበት ይደነግጋሉ። በረቂቅ ደንቡ የተቀመጠው ትርጉም የበለጸጉ ሃገራትን ታሳቢ ያደረገ መሆኑ እና ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ባለሙያዎች እውቅና ባለው የትምህርት ተቋም ስልጠና ላያገኙ ስለሚችል ገደቡ የሃገሪቱን ሁኔታ ያላገናዘበ ነዉ። ይህ ትርጉም በሕግ የሚቋቋሙና የመንግስት አስተዳደራዊ ስልጣን የሚሰጣቸውን የሙያ ማኅበራት ከሚመለከት ሕግ ትርጉም የተወሰደ እናም ከዛ ውጭ ያሉ ድርጅቶችን ያላገናዘበ ነዉ።

ከዚህ በተጨማሪም ደንቡ አዋጁን ለማስፈፀም የወጣ እና በደረጃም ከአዋጁ በታች ስለሆነ በአዋጁ ስር የሌለ አዲስ ገደብ ማስቀመጥ የለበትም። በአንፃሩ አዋጁ በሚረቀቅበት ጊዜ ሙያ ማኅበራት ከሌላ የሲቪል ማኅበር አይነቶች ሲነጻጸሩ ያነሰም የበዛም መብት እንደማይኖራቸው የሥራ ቡድኑ በግልጽ የተወያየበትና ይህም አዋጁ ውስጥ እንዲንጸባረቅ ያደረገ ከመሆኑ አንጻር በደንቡ ውስጥ ከአዋጁ የተለየና አዲስ ገደቦችን የሚጥል ድንጋጌ መጨመሩ አላስፈላጊ ነዉ። ስለሆነም የረቂቅ ደንቡ አንቀፅ 7(1) ከላይ የተዘረዘሩትን ምክንያቶች ከግምት ዉስጥ በማስገባት ሊሻሻሉ ይገባል።

### 3.2.4. ከመንግስት ጋር ተቀራርቦ ስለመስራት እና ድጋፍ (አንቀፅ 7(3))

ረቂቅ ደንቡ የሙያ ማኅበራትን ውጤታማነት ለማሳደግ ማኅበራቱ የሚሰማሩበትን የሙያ ዘርፍ የሚመሩ የመንግስት አካላት "ከሙያ ማኅበራቱ ጋር በቅርበት መስራትና ድጋፍ ማድረግ" እንዳለባቸው ያስቀምጣል። ረቂቅ ደንቡ በጥቅሉ "በቅርበት መስራት እና ድጋፍ ማድረግ አለባቸው" ከማለት ባሻገር በምን ሁኔታዎች እና እንዴት ትብብር እና ድጋፍ እንደሚደረግ ዝርዝር አንቀጾችን አላስቀመጠም። ይህ ደግሞ የመንግስት አካላት በሙያ ማህበራት የስራ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ጣልቃ እንዲገቡ በር የሚከፍት ሊሆን ይችላል። ከዚህ ጋር ተያይዞ አለም አቀፉ የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ስምምነት እንዲሁም የአፍሪካ የሰዎች እና የህዝቦች ቻርተር በመደራጀት ነፃነት ላይ የሚደረግ ማንኛውም ገደብ "በግልፅ በሕግ መቀመጥ" እንዳለበት ይገልፃሉ። ገደብ ለማድረግ የወጣው ሕግ የግልፅነት መለኪያን የማያልፍ ከሆነ እና ግልፅነት የጎደለው በሚሆንበት ጊዜ ድርጅቶች አላማዎቻቸውን እና ስራዎቻቸውን በነፃነት መወሰን እንደሚችሉ የአፍሪካ ኮሚሽን አስምሮበታል[7]።

ስለሆነም ረቂቅ ደንቡ የሙያ ዘርፍ መሪ የመንግስት አካላት ለሙያ ማኅበራት ድጋፍ የማድረግ ግዴታ ዕንዳለባቸዉ በሚገልፅ መልኩ በሙያ ማኅበራት እና በመሪ የመንግስት አካላት መካከል ስለሚደረጉ ትብብሮች እና ድጋፎች ዝርዝር ድንጋጌዎችን አካቶ ሊሻሻል ይገባል። ኤጀንሲው "ከሙያ ማኅበራቱ ጋር በቅርበት መስራትና ድጋፍ ማድረግ" የሚለው መርህ የግድ ያስፈልጋል የሚል ጽኑ እምነት ያለው ከሆነ በሲቪል ማህበረሰብ ድረጅቶች መመርያ ይልቅ ይህን ግዴታ በዝርዝር የሚያስቀምጥ አዋጅ በማርቀቅ ወይም የሚኒስቴሮች መስርያ ቤቶችን የሚያቋቁመውን አዋጅ የመከለስ ስራ በማስጀመር ሊወጣው የሚገባው ሃላፊነት ነው።

[7] በአፍሪካየመደራጀትእናየመሰብሰብነፃነትመመሪያ፣ አንቀፅ-23።

### 3.2.5. በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ሕጋዊ አስመስሎ ስለማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ ስለመርዳት (አንቀፅ 13)

ረቂቅ ደንቡ ኤጀንሲው “ስልጣን ካለው የመንግስት አካል” ጋር በመተባበር በዘርፉ በወንጀል የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረትን ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀሎችን ለመከላከል ስጋቶችን የመለየትና “የጎን ለጎን ምርመራዎችን” የማከናወን ስራ እንደሚሰራ ይገልፃል። ይህ አንቀፅ ሕገ ወጥ የገንዘብ ዝውውርን እና ሽብርተኝነት በገንዘብ የመደገፍ ወንጀሎችን ለመከላከል ለኤጀንሲው እና “ስልጣን ላለው አካል” ስጋቶችን የመለየት እና “ጎን ለጎን” ምርመራ እንዲያደርጉ እነዲሁም አስፈላጊ መመሪያዎችን እንዲያወጡ እና እንዲያስፈፅሙ የሚፈቅደውን የቀድሞውን ሕግ ድንጋጌ ከሞላ ጎደል እንዳለ ያስቀጠለ ነው። በተጨማሪም የረቂቅ ደንቡ አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ2 ለኤጀንሲው በአዋጁ ያልተሰጠውን መመርያ የማውጣት ስልጣን ማጎናፀፉ ከስር ሕገወጥ የገንዘብ ዝውውር ወይም ሽብርተኝነትን በሚመለከት ከተቀመጡት ጉዳዮች በተጨማሪ መሠረታዊ የሕጋዊነት ጥያቄ ያስነሳል።

በመጀመርያ እይታ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ዋና ችግር የቃላት አጣጣልና አላስፈላጊነት (Superfluousness) መሆኑ ቢመስልም የወንጀልን ውጤት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ከሚመለከቱ ቴክኒካዊ ተለምዶዎች አንፃር ሲታይ ግን ብዙ ክፍተቶች እንዳለበት መረዳት ይቻላል። በመጀመሪያ ደረጃ ይህ ድንጋጌ የስጋት መለየት እና የጎን ለጎን ምርመራ ሂደቶች በምን መሰረት እና ምክንያት እንደሚካሄዱ እንዲሁም በዚህ ሂደት ኤጀንሲው እና የሚመለከተው የመንግስት አካል ሊከተሏቸው ስለሚገባ ስነ-ስርዓቶች በግልፅ እና ጥበቃ በሚሰጥ ደረጃ አልተቀመጠም። ይህ አካሄድ የሲቪልማኅበረሰብድርጅቶችን በሌላ ሕግ ከተቀመጡ ወይም ከሚቀመጡ የወንጀልና ሌላ ስነ-ስርዓት ጥበቃዎች ውጭ የማድረግ አሰራር ሊፈጥር ከመቻሉም በተጨማሪ የወንጀልን ውጤት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን የሚመለከቱ ሕግጋትና አሰራሮች የተቆራረጡና የተዝረከረኩ እንዲሆኑ ያደርጋል። ሁለተኛ ድንጋጌው ሁሉም የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በእኩል ደረጃ ለሕገ ወጥ የገንዘብ ዝውውር ወይም ሽብርተኝነትን በገነዘብ መደገፍ ድርጊቶች ተጋላጭ አድርጎ ተመሳሳይ ቁጥጥር ጥሎባቸዋል። ይህ አይነት አሰራር መንግስታት ሕገ ወጥ የገንዘብ ዝውውር፣ ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን እና ሌሎች የአለም አቀፍ የገንዘብ ስርዓት ስጋቶችን ለመከላከል ያቋቋሙት ሕገወጥ የገንዘብ ዝውውር ቁጥጥር ግብረ ሀይል ካከናወናቸው ጥናቶች አንጻር ሲታይ ተጋላጭነትን መሰረት ያደረገ የቁጥጥር ስርዐት አስፈላጊነት ላይ የተደረሰባቸውን ድምዳሜዎችና ምርጥ ልምዶች የጣረሳል።[8] በተጨማሪም ረቂቅ ደንቡ ኤጀንሲው በወንጀል የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረትን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ስጋቶች ለመከላከል የሚያስችሉ አሰራሮች የድርጅቶች የራስ ቁጥጥር ስርዓት የሚካተቱበትን ሁኔታ እንዲያመቻች መፍቀዱ መንግስት ስጋቶች በሌሉበት ሁኔታዎችም ጭምር በድርጅቶች የውስጥ አስተዳደር ጣልቃ እንዲገባ እድል የሚሰጥ ነው።

አለም አቀፉ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት እንዲሁም የአፍሪካ የሰዎች እና የህዝቦች ቻርተር በመደራጀት መብት ላይ የሚደረግ ማንኛውም ገደብ “በሕግ መደንገግ” እንዳለበት ያስቀምጣሉ። ረቂቅ ደንቡ ህገ-መሰረት የሌለው መመርያ የማውጣት ስልጣን ለኤጀንሲው ከመስጠቱ በተጨማሪ መቼ እና እንዴት የስጋት መለየት እና የጎን ለጎን ምርመራ እንደሚደረግ ዝርዝር ድንጋጌዎችን ባለማካተቱ ድርጅቶች ግዴታቸውን እንዴት መወጣት እንዳለባቸው ለማወቅ የሚቸገሩ ሲሆን በአለም

[8] Financial Action Task Force (FATF), Risk of Terrorist Abuse in Non-Profit Organisations (FATF/OECD June 2014)ይመልከቱ።

አቀፍ መስፈርቶች የተቀመጠውን ገደቦችን በግልፅ ሕግ የማስቀመጥ መስፈርት አያሟላም። በአንፃሩ የገንዘብ ነክ ጉዳዮች መመሪያ ሀገራት ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ድርጊቶችን ለመከላከል ጥቅል የሆነ ማዕቀፍ ከማስቀመጥ ይልቅ "ለስጋት ተጋላጭ በሆኑ ተቋማት ላይ ትኩረት በማድረግ ተመጣጣኝ ርምጃዎችን" መውሰድ ላይ ትኩረቱን ያደረገ ተጋላጭነትን መሰረት ያደረገ ዘዴ ትግበራ ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለባቸው ይመክራል። የአፍሪካ ኮሚሽን ፍኖተ ካርታ መንግስት በድርጅቶች ላይ የሚያደርገው ቁጥጥር "አስፈላጊ እና ዝቅተኛ የሆኑ የውስጥ አስተዳደር አደረጃጀት ወይም መስፈርቶች ማስቀመጥ ላይ ብቻ" ሊወሰን እንደሚገባ ይገልፃል።[9] በረቂቅ ደንቡ በወንጀል የተገኘን ገንዘብ ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርን በገንዘብ የመርዳት ድርጊትን ለመከላከል የተቀመጡ ድንጋጌዎች ከዝቅተኛው መስፈርት በላይ በመሆናቸው የድርጅቶችን የውስጥ አስተዳደር ነፃነት የሚፈታተኑ ናቸው። ስለሆነም አንቀፅ 13 ከረቂቅ ደንቡ መውጣት አለበት ወይም ደግሞ ስለ ስጋት መለየት እና ምርመራ ሂደቶች ጥልቅ ጥናት ላይ የተመሰረቱ ዝርዝር ድንጋጌዎችን በማካተት ለድርጅቶች ጥበቃ በሚያደርግ መልኩ እንደገና ሊሻሻል ይገባል።

### 3.2.6. ንብረት ሽያጭና ስጦታን በሚመለከት የተቀመጡ አዲስ ገደቦች እና አስተዳደራዊ ሸክሞች (አንቀፅ 14)

የረቂቅደንቡአንቀፅ 14 ከስር የተቀመጡ ሊታለፉ የማይገባቸውን ፍሬነገሮች ከመያዙ በተጨማሪ አንቀጹ ባጠቃላይ ግልጽነት የጎደለውና የዘፈቀደ ጣልቃ-ገብነትን የሚጋብዝ አቀራረጽ ያካተተ ነዉ። ለምሳሌ የአንቀፅ 14 ንዑስ (1) እና (5) ከቃል አጣጣልና የሕግ አተረጓጎም አንጻር ዋጋ የማይጨምሩ ወይም አላስፈላጊ (superfluous) ቢሆኑም አስፈጻሚ አካላት ተጨማሪ ድንጋጌ ወይም ቅድመ-ሁኔታ አድርገው የሚተረጉሙባቸውን እድሎች ከመክፈታቸው አንጻር አላስፈላጊነታቸው (Superfluousness) ከሕግ ማርቀቅ ጥራትና ደረጃ ባለፈ የዘፈቀደ ጣልቃ-ገብነት አደጋ የሚጋብዙ ናቸዉ። አንቀፅ (1) እና (5) ከስር ከተቀመጡ ሊታለፉ የማይገባቸው መሰረታዊ የመደራጀት መብትና የህጋዊነት ጥያቄ ጋር አንድ ላይ ሲታዩ የሚጥሉት አደጋ ንድፈ-ሃሳባዊ ብቻ እንዳልሆነ ግልጽ ይሆናል።

#### *ሀ. የሽያጭ ወይም የስጦታ ውልን ስለማሳወቅ (አንቀፅ 14(2))*

ረቂቅ ደንቡ በአንቀፅ 14(2) የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ንብረት ለማስተላለፍ የሚያስችላቸውን የሽያጭ ወይም የስጦታ ውል በተዋዋሉ በአስራ አምስት ቀን ጊዜ ውስጥ ይህንኑ የሚያሳይ መረጃ ለኤጀንሲው እንዲያሳውቁ ያስገድዳል። ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ለማንኛውም ትልቅም ይሁን ትንሽ ሽያጭ ወይም ስጦታ ለኤጀንሲው እንዲያሳውቁ ግዴታ መጣል በድርጅቶች ላይ ጫና የሚያበዛ ነው። ይልቁንም ይህ አይነቱ ሽያጭ ወይም ስጦታ ድርጅቶች በአመቱ መጨረሻ ለኤጀንሲው በሚያስገቡት የሂሳብ ሪፖርት መካተት የሚችል ነው። ድርጅቶች እያንዳንዱን ሽያጭ ወይም ስጦታ እንዲያሳውቁ ማስገደድ አራቱን ቅቡልነት ያላቸው የተፈቀዱ የመንግስት አላማዎች ለማሳካት የሚተገበር ዝቅተኛው የክልከላ ዘዴ ባለመሆኑ "በዴሞክራሲያዊ ማኅበረሰብ" ውስጥ ሊደረግ የሚችል አስፈላጊ ገደብ አይደለም።የአፍሪካ የሰዎች እና የህዝቦች ቻርተር ፍኖተ ካርታ ሪፖርት የማድረጊያ ቅድመ ሁኔታዎች "ቀላል እና በድርጅቶች ላይ ጫና የማይፈጥሩ" መሆን እንዳለባቸው ይጠቅሳል።[10] ማንኛውም የሚደረግ ገደብ በዴሞክራሲያዊ ማኅበረሰብ ውስጥ አስፈላጊ ነው ሊባል የሚችለው አራቱን ቅቡልነት ያላቸው

---

[9]በአፍሪካየመደራጀትእናየመሰብሰብነፃነትመመሪያ፣ አንቀፅ. 31።

[10]በአፍሪካየመደራጀትእናየመሰብሰብነፃነትመመሪያ፣ አንቀፅ 48።

የመንግስት አላማዎች ዝቅተኛ በሆነ የክልከላ ዘዴ ለማሳካት የተደረገ ሲሆን ነው።[11] ስለሆነም አንቀፅ 14(2) ድርጅቶች የሽያጭ ወይም የስጦታ ዉሎችን በአመታዊ ሪፖርታቸዉ አካተዉ እንዲያቀርቡ በሚያስገድድ መልኩ ሊሻሻል ይገባል።

## ለ. የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ወይም ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን ተሸከርካሪዎች ስለመሸጥ (አንቀፅ 14(3))

ረቂቅ ደንቡ በአንቀፅ 14(3) የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የማይንቀሳቀስ ንብረት ወይም ከፍተኛ ዋጋ ያለቸውን ተሸከርካሪዎች በሽያጭ ባገኙ ወይም ባስተላለፉ ጊዜ ይህንን ግብይት የሚያሳይ “ዝርዝር” መረጃ በአመታዊ ሪፖርታቸው ማካተት እንዳለባቸው ይገልፃል። ይሁን እንጅ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ሊያከናውኑ ያሰቡት ተግባር የሕግ ጥሰት መሆኑን ወይም አለመሆኑን በቀላሉ ሊረዱት በሚያስችል ደረጃ ግልፅ ባለመሆኑ ምክንያት ማኝኛውም ገደብ በሕግ ሊቀመጥ ይገባል የሚለውን መለኪያ አያሟላም። በአለም አቀፉ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት እንዲሁም በአፍሪካ የሰዎች እና የህዝቦች ቻርተር የተቀመጠውን ማንኛውም የሚደረግ ገደብ “በሕግ ሊቀመጥ” ይባል የሚለውን ቅድመ ሁኔታ ለማሟላት የሚደረገው ገደብ ግለሰቦች ወይም የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ሊያከናውኑ ያሰቡት ተግባር የሕግ ጥሰት መሆኑን ወይም አለመሆኑን በቀላሉ ሊረዱት በሚያስችል ደረጃ ግልፅ ሆኖ ሊቀመጥ ይገባል። ከዚህ በተጨማሪም የአፍሪካ ኮሚሽን ፍኖተ ካርታ ሪፖርት የማድረግ ግዴታዎች “አላስፈላጊ ጫና የማያስከትሉ እና ቀላል” መሆን እናዳለባቸው ያስቀምጣል።[12] ስለሆነም ይህ ድንጋጌ መሠረታዊ የህጋዊነት ችግር ያለበትና አለማቀፍ መርሆችን የሚጣረስ በመሆኑ እንደገና ግልፅ ሆኖ ሊከለስ ወይም ሊሰረዝ ይገባል።

## ሐ. ንብረትን በስጦታ ስለማስተላለፍ (አንቀፅ 14(6))

የረቂቅ ደንቡ አንቀፅ 14(6) ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ንብረትን በስጦታ ማስተላለፍ የሚችሉት ለሌላ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ወይም ለመንግስት ተቋም ብቻ እንደሆነ ይደነግጋል። ይህ ድንጋጌ በአዋጁ ያልተካተተና ሌላ የህግ መሰረት የሌለው ከመሆኑም በተጨማሪ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን ስራዎች እና የፈንድ አጠቃቀም የሚገድብ ነው። ለምሳሌ አንድ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ፈንዱን መድህኒት ወይም መፅሀፍት ለሚፈልጉ አካላት በስጦታ መልክ ሊጠቀመው ቢፈልግ ሊፈቀድለት ይገባል። በሲቪል ማኅበረሰብ ተቋማት ስጦታ ሊያደርጉላቸው የሚችሉ አካላትን በዚህ ሁኔታ መገደብ በአንድ ዴሞክራሲያዊ ማኅበረሰብ ውስጥ አራቱን ቅቡልነት ያላቸው የመንግስት አላማዎች ለማሳካት ሊደረጉ ከሚችሉ አስፈላጊ ገደቦች መካከል አይካተትም። በመንግስት በኩል በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ገንዘባቸውን ላልተገቡ አካላት እንዳያስተላልፉ ስጋቶች ቢኖሩም አዋጅ ቁጥር 1113/2011 ድርጅቶች በአገልግሎት ክፍያ ወይም ደሞዝ መልክ ካልሆነ በስተቀር ለአባላት ወይም ለሰራተኞች ገንዘብ ማስተላለፍ እንደማይችሉ በአንቀፅ 60 (1)(መ) የተቀመጠ በመሆኑ ስጋቱን የሚቀርፍ ነው። ሲቪል ማኅበረሰብ ማኅበራት የፈለጉትን ተግባራት እንዲያከናውኑ ሊፈቀድላቸው ይገባል። ማንኛውም በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ስራ ላይ የሚደረግ ገደብ ግልፅ በሆነ ሕግ መቀመጥ ያለበት ሲሆን ይህ ገደብ በዴሞክራሲያዊ ማኅበረሰብ ውስጥ አራቱን ቅቡልነት ያላቸው የመንግስት አላማዎች ለማሳካት የተፈቀደ ገደብ ሊሆን ይገባል። ስለሆነም አንቀፅ 14(6) ከረቂቅ ደንቡ ሊወጣ ይገባል።

---

[11]የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ፣ ሰላማዊ ስብሰባ የማድረግ እና የመደራጀት ነፃነት ልዩ ሪፖርት፣*Maina Kiai*, U.N. Doc.A/HRC/20/27 (2012) [ከዚህ ብኋላ “የተባበሩትመንግስታት የመደራጀትነፃነትሪፖርት”]አንቀፅ 17 ይመልከቱ።

[12]የተባበሩትመንግስታት የመደራጀትነፃነትሪፖርት።

### 3.2.7. ለሶስተኛ ወገን ጥቅም በተቋቋሙ ድርጅቶች ላይ ስለሚደረግ ክትትል (አንቀፅ 15(6))

የረቂቅ ደንቡ አንቀፅ 15(6) ለሶስተኛ ወገን ጥቅም የተቋቋሙ ድርጅቶች “የተሰማሩበት የገቢ ማስገኛ ሥራው ለታለመለት የበጎ አድራጎት አላማ እየዋለና በተገቢው መንገድ እየተመራ” መሆኑን ኤጀንሲው እንዲከታተል ስልጣን ሰጥቶታል። ይሁን እንጅ ይህ ድንጋጌ ለመንግስት በአግባቡ ያልተገደበ ሰፊ የቁጥጥር ስልጣን የሰጠ እንዲሁም የመንግስትን ቅቡልነት ያለው አላማ ለማሳካት የተደረገ ዝቅተኛው የክልከላ ዘዴ ባለመሆኑ በአፍሪካ የሰዎች እና የህዝቦች ቻርተር እና በአለም አቀፉ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ድንጋጌ ከተቀመጡት ቅድመ ሁኔታች ጋር አብሮ አይሄድም። በአዋጁ መሰረት የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ለኤጀንሲው የሚያስገቡት አመታዊ የገንዘብ እንቅስቃሴ ሪፖርት የድርጅቶች ስለሚያገኙት ገቢ ትክክለኛነት በቂ መረጃ ማካተት እንዳለባቸው ተቀምጧል። የመንግስት የቁጥጥር ሥልጣን “በጥንቃቄ ሊወሰን” ይገባል።[13] በተጨማሪም ማንኛውም ለመንግስት የሚሰጥ የቁጥጥር ስልጣን አራቱን የመንግስት ቅቡልነት ያላቸው የተፈቀዱ አላማዎች ለማሳካት ዝቅተኛው የክልከላ ዘዴ ሊሆን ይገባል። ስለሆነም የረቂቅ ደንቡ አንቀፅ 15(6) የኤጀንሲዉን ስልጣን በዝርዝር በሚገድብ መልኩ ሊቀመጥ ወይም ከረቂቅ ደንቡ ሊወጣ ይገባል።

### 3.2.8. ስለ ፕሮጀክት ስምምነት (አንቀፅ 21)

ረቂቅ ደንቡ ኤጀንሲው እና ሴክተር መስሪያ ቤቶች በአዋጁ በተሰጣቸው ስልጣን እና ተግባራት ዙሪያ ከሚሰማሩ ድርጅቶች ጋር የፕሮጀክት ስምምነት የመፈረም ስልጣን እንዳላቸው ያስቀምጣል። ከዚህ አኳያ ረቂቅ ደንቡ ከአዋጁ ጋር የተጣጣመ ቢሆንም በደንቡ አንቀፅ 21 ንዑስ (2) የተቀመጠው ፕሮጀክት ስምምነት የሚፈራረሙ ሴክተር መስሪያ ቤቶች “ስምምነቱን በአጭር ጊዜ ውስጥ በመፈራረም ድርጅቶች ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ ይኖርባቸዋል” የሚለው ድንጋጌ ግን የተለያዩ ችግሮችን ሊያስነሳ ይችላል። ድንጋጌው በዋናነት የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በአፋጣኝ ወደ ስራ እንዲገቡ ለማድረግ የተቀረጸ ቢመስልም በተግባር ሴክተር መስሪያ ቤቶች ላይ ምንም አይነት ሕጋዊ ውጤት የሚያስከትል ግዴታ ካለመጣሉም በተጨማሪ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ከሴክተር መስሪያ ቤቶች ጋር ስምምነት ካልፈጸሙ ወደ ስራ መግባት እንደማይችሉ ያመላክታል። ይህ አቀራረጽ በአንድ በኩል ወደ ስራ ለመግባት የፕሮጀክት ስምምነት አስገዳጅ መስፈርት እንደሆነ እንደሚያስቀምጥ ግንዛቤ ሊወሰድ ሲችል በሌላ በኩል ደግሞ በተለይ በአተገባበሩ ሂደት እንደ ቅድመ ሁኔታ ተወስዶ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ያለ ፕሮጀክት ስምምነት ስራ እንዳይሰሩ ወይም ወደ ስራ በሚገቡበት ሂደት ላላስፈላጊ እንግልት ሊዳረጉ ይችላል። በመጀመርያው አተረጓጎም ድንጋጌውን ሕጋዊነት የሌለው ቅድመ ሁኔታ ወይም ክልከላ ሲያደርገው ሁለተኛው አተረጓጎም ደግሞ ግልጽነት የጎደለውና የዘፈቀደ ጣልቃ-ገብነትን የሚጋብዝ ያደርገዋል። ይህ ድንጋጌ አዋጁ ለመፍታት የሞከራቸዉን ዋና ዋና ማነቆዎች አንዱን መልሶ ሊያመጣ የሚችል በመሆኑ እና ከአለም አቀፍ የመመዘኛ መስፈርቶች ጋር የሚጋጭ በመሆኑ አንቀፅ 21(2) ከረቂቅ ደንቡ ቢወጣ የተሻለ ነው።

### 3.2.9. ልዩ ድጋፍ የሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች (አንቀፅ 24)

የረቂቅ ደንቡ አንቀፅ 24 ማንኛውምድርጅትበሚያከናውነውስራውስጥየሴቶች፣ህፃናት፣አካል ጉዳተኞች፣አረጋውያንና ሌሎች ልዩ ድጋፍ የሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ጥቅም ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራትን በስራ እና በበጀት እቅድ ውስጥ በመያዝና የአካቶ መፈፀም ስርዓትን ቀርፀው መተግበር እንዲሁም የአቅም ውስንነት ያለባቸውን ድርጅቶች በገንዘብ፣በቁሳቁስ ወይም

[13]በአፍሪካየመደራጀትእናየመሰብሰብነፃነትመመሪያ፣አንቀፅ 33።

በእውቀት የመደገፍ ግዴታ እንዳለባቸው በመደንገግ ይህኑ በዓመታዊ ሪፖርታቸው ማካተት እንደሚገባቸውና ሌላ ተያያዥ ግዴታዎችን እንዲፈጽሙ ያስገድዳል። ይህ ድንጋጌ በአዋጁ ያልተጣለ ግዴታን በመጫኑ ምክንያት ሕጋዊ መሰረትና ሕገ-መንግስታዊነት የሌለው ከመሆኑም በተጨማሪ እንደ "ጥቅም ማረጋገጥ"፣ "የሚያስችሉ ተግባራት"፣ "መብትና ጥቅም ከማስጠበቅ አኳያ"፣ "ልዩድ ጋፍ የሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ጥቅም አካተው እየፈፀሙ መሆናቸው" ያሉ ግልፅነት የሌላቸውና የዘፈቀደ ጣልቃ ገብነት በሚጋብዙ አገላለጾች የተሞላ መሆኑ ከሕጋዊነት መርህ አንፃር የላቀ ጉድለት ነው።

አንቀጹ የሚጥላቸው ግዴታዎች የመደራጀት መብትን ሕጋዊ ባልሆነና ኢ-ሕገ-መንግስታዊ በሆነ መንገድ ከመገደቡ በተጨማሪ የሚያስቀምጣቸው ግዴታዎች የአስተያየትና ሀሳብን የመያዝና የመግለጽ ነፃነትን የሚገድቡ ስለሆነ ከጀርባቸው ያሉ የፖሊሲ ስሌቶች ዲሞክራስያዊ በሆነ ሂደት ተወካዮች ምክር ቤት እናም ለሕዝባዊ ውይይት መቅረብ ያለባቸው ጉዳዮች እንጂ በደንብ ሊደነገጉ የሚችሉ ጉዳዮች አይደሉም። የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ይህን እንዲያደርጉ በሕግ ከማስገደድ ይልቅ ድርጅቶች በራሳቸዉ ተነሳሽነት በፅነኝህ ተግባራት ላይ እንዲሳተፉ መደገፍ እና ማበረታት የተሸለዉ አማራጭ ነዉ። ኤጀንሲው መዋቅራዊ አለመመጣጠን የሚያጋጥማቸው ቡድኖችን መብት ለመደገፍና ለማስጠበቅ ያደረገው ጥረት አበረታች ቢሆንም ይህን አላማ የሚወሰድ እርምጃ ዋናውን አዋጅ የማይጥስ እንዲሁም ሕገ መንግስታዊና የአለማቀፍ ሰብዓዊ መብቶችን በሚያከብር መልኩ የማሳካት ግዴታ ስላለበት አንቀፅ 24ን ከዚህ ረቂቅ ማስቀረት አለበት።

### 3.2.10. ስለ ሲቪል ማኅበራት ፈንድ (አንቀፅ 25)

የረቂቅ ደንቡ አንቀፅ 25 አገራዊና ዓለም አቀፋዊ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ለሲቪል ማኅበረሰብ ፈንድ እርዳታና ድጋፍ ሊያደርጉ ይችላሉ በማለት ይደነግጋል። ይሁን እንጅ የሲቪል ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 113/2011 በአነቀጽ 86(4) ስር የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ለሲቪል ማኅበራት ፈንድ መዋጮ ማድረግ እንደማይችሉ ይገልፃል። ይህ የረቂቅ ደንቡ አንቀፅ ከአዋጁ ጋር የሚጣረስ ከመሆኑም ባሻገር የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች መዋጮ ማድረግ የተፈቀደላቸው ስለመሆኑ ወይም አለመሆኑ ብዥታዎችን የሚፈጥር በመሆኑ ገደቦች በሕግ ግልፅ በሆነ መንገድ መቀመጥ አለባቸው የሚለውን መስፈርት የሚጥስ ነው። በተጨማሪም የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ለሲቪል ማኅበራት ፈንድ መዋጮ እንዲያደርጉ መፍቀድ መዋጮ ያደረጉ ድርጅቶች ከሲቪል ማኅበራት ኤጀንሲ ጋር ከሚኖራቸው ጉዳይ ጋር ተያይዞ ግልፅ ወይም ተዘዋዋሪ የጥቅም ግጭት የሚያስከትል ነው። ለምሳሌ ከፍተኛ መዋጮ ያደረገን የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝም ቅጣት በማይጥልበት ጊዜ የጥቅም ግጭት ሊነሳ ይችላል።

በአለም አቀፉ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት እንዲሁም በአፍሪካ የሰዎች እና የህዝቦች ቻርተር የተቀመጠውን ማንኛውም የሚደረግ ገደብ "በሕግ ሊቀመጥ" ይባል የሚለውን ቅድመ ሁኔታ ለማሟላት የሚደረገው ገደብ ግለሰቦች ወይም የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ሊያከናውኑ ያሰቡት ተግባር የሕግ ጥሰት መሆኑን ወይም አለመሆኑን በቀላሉ ሊረዱት በሚያስችል ደረጃ ግልፅ ሆኖ ሊቀመጥ ይገባል። ሁለት እና ከዚያ በላይ እርስ በእርሳቸው የሚጣረሱ ድንጋጌዎች በሚኖሩ ጊዜ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የሚያከናውኗቸው ተግባራት የሕግ ጥሰት መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ማረጋገጥ ስለማይችሉ በአለም አቀፍ መስፈርቶች የተቀመጠው ገደቦች በግልፅ በሕግ መቀመጥ አለባቸው የሚለውን ቅድመ ሁኔታ የማይሟላ ይሆናል። ስለሆነም በረቂቅ ደንቡ አንቀፅ 23 "መንግስታዊ ያልሆኑ" ድርጅቶች ለሲቪል ማኅበራት ፈንድ መዋጮ ማድረግ ይችላሉ የሚለው መውጣት አለበት።